**ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች**

(ቅዳሜ—ሁለተኛ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)

መልእክት አምስት

**የእውነት በአንድ ልብ መሆን**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ሐዋ. 1፡14፤ 2፡46፤ 4፡24፤ 5፡12፤ 15፡25፤ ሮሜ 15፡6

**I. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛው በአንድ ልብ መሆን የአካሉ አንድነት ተግባራዊ ልምምድ ነው፣ ይህም የመንፈስ አንድነት ነው—ኤፌ. 4፡3-6፡-**

ሀ. ከኤፌሶን 4፡4-6 አንድነትን በተግባር መለማመዳችን በቤተ ክርስቲያን የአንድነት ባሕሪ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማየት እንችላለን፡- አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ አምላክ፣ አንድ አካል፣ አንድ እምነት፣ አንድ ጥምቀት እና አንድ ተስፋ።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእውነተኛው በአንድ ልብ የመሆን ተግባራዊው ልምምድ የአንድነት ትግበራ ነው—ሐዋ. 1፡14፤ 2፡46።

ሐ. የአንድነት ተግባራዊ ልምምድ በአንድ ልብ ከመሆን ጋር ነው፤ አንድነትን በተግባር ሲለማመዱት በአንድ ልብ መሆን ይሆናል—15፡25፡-

1. በዮሐንስ ወንጌል ጌታ ለአንድነት አጽንኦት ሰጥቷል፣ በሐዋርያት ሥራ ላይ ግን በአንድ ልብ መሆን አጽንኦት ተሰጥቶታል—የሐ. 10፡30፤ 17፡11፣ 21-23፤ ሐዋ. 1፡14፤ 2፡46፤ 4፡24፤ 15፡25።
2. ወንጌላትን እና የሐዋርያት ሥራን የሚለየው ምልክት በመቶ ሃያዎቹ መካከል የነበረው በአንድ ልብ መሆን ነው—1፡14፡-
   - ሀ. በአካሉ ውስጥ አንድ ሆነው ነበር፣ በዚያም አንድነት ውስጥ በአንድ ልብ በመጸለይ በጽናት ባለማቋረጥ ቀጠሉ—ኤፌ 4፡3-6፤ ሐዋ 1፡14።
   - ለ. ሐዋርያት እና አማኞች የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት በተግባር ሲለማመዱ በአንድ ልብ ሆነው በተግባር ተለማመዱት—2፡46፤ 4፡24፤ 5፡12።

መ. በአንድ ልብ መሆን የአንድነት ማዕከላዊው፣ በጣም አስፈላጊው እና ዋናው ነገር ነው—ኤፌ. 4፡3፤ ሐዋ. 4፡24፤ ሮሜ 15፡6፡-

1. አንድነት እንደ የሰውነት አካል ነው፣ በአንድ ልብ መሆን ደግሞ በሰውነት አካል ውስጥ እንዳለ ልብ ነው።
2. መንፈሳዊ በሽታችን ልክ በሰውነት አካል ውስጥ እንዳለ የልብ በሽታ ነው፤ በመካከላችን ያለው በሽታ በአንድ ልብ መሆን በአጥጋቢ ሁኔታ ስለሌለን ነው፣ ከዚህም የተነሣ አንድነትን የምንጠብቀው በታመመ "ልብ" ነው።

**II. በአንድ ልብ መሆን የሚያመለክተው በውስጣዊ ማንነታችን፣ በሃሳባችን እና በፈቃዳችን ያለውን ኅብር ነው—ሐዋ. 1፡14፡-**

ሀ. በሐዋርያት 1፡14 *ሆሞቱማዶን* የሚለው የግሪክ ቃል በአንድ ልብ መሆንን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል፡-

1. ይህ ቃል የመጣው *ሆሞ* "ተመሳሳይ" እና *ቱምስ* "ሃሳብ፣ ፈቃድ፣ ዓላማ (ነፍስ፣ ልብ)" ከሚሉት ቃላት ሲሆን፣ የሚያመለክተውም በአንድ ሰው መላ ማንነት ውስጥ ያለውን የውስጣዊ ስሜት ኅብርን ነው።
2. በነፍሳችን እና በልባችን ዙሪያ እና ውስጥ፣ ከአንድ ዓላማ ጋር በአንድ ሃሳብ እና በአንድ ፈቃድ ውስጥ መሆን አለብን፤ ይህም መላው ማንነታችንን ያካትታል ማለት ነው።

ለ. በማቴዎስ 18፡19 የግሪኩ ቃል *ሱምፎኔኦ* በአንድ ልብ መሆንን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል፡-

1. የቃሉ ትርጉም "በኅብር ወይም በአንድ ልብ መሆን" ሲሆን፣ የሚያመለክተውም በኅብር የሆኑ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ወይም ድምጾችን ነው።
2. በአንድ ልብ መሆን ወይም በአማኞች መካከል ያለው የውስጥ ስሜት ኅብር ልክ በኅብር እንደተሞላ ዜማ ነው።
3. በአንድ ልብ መሆን ሲኖረን ለእግዚአብሔር ዜማ እንሆናለን፤ በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በድምጽ፣ በዜማም ግጥም እንሆናለን።

**III. በአንድ ልብ መሆንን የሚያስቀጥለው የሐዋርያት ትምህርት ነው—ሐዋ. 2፡42፤46፡-**

ሀ. የአንድነት ተግባራዊ ልምምድ—በአንድ ልብ መሆን—በሐዋርያት ትምህርት መሠረት ነው—ቁ. 42።

ለ. በአማኞች መካከል በአንድ ልብ መሆን እንደነበር እና በአንድ ልብ የነበሩት ሁሉ ደግሞ በሐዋርያት ትምህርት በጽናት እንደቀጠሉ የሐዋርያት ሥራ ይነግረናል።

ሐ. ሐዋርያት በየስፍራው እና በየአብያተ ክርስቲያናቱ ላሉ ቅዱሳን ሁሉ አንድ አይነት ነገር አስተማሯቸው—1 ቆሮ. 4፡17፤ 7፡17፤ 11፡16፤ 14፡33-34፦

1. እኛም በምድር ሁሉ፣ በየአገሩ፣ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ አይነት ነገር ማስተማር አለብን—ማቴ 28፡19-20።
2. አንድ ትምህርት ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ፣ ለሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ግን ጥሩ ያልሆነ ትምህርት ነው የሚል ሃሳብ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የለም፤ ይልቁንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ትምህርቶቹን በመቀበል ተመሳሳይ እንደነበሩ አዲስ ኪዳን ይገልጣል—ቲቶ 1፡9።

## IV. በአንድ ልብ መሆንን በተግባር ስንለማመድ ከአንድ ነፍስ ጋር በአንድ መንፈስ መሆንን መማር አለብን—ፊልጵ. 1፡27፦

ሀ. በአንድ ልብ እንሆን ዘንድ ወደ መንፈሳችን መዞር እና በአንድ መንፈስ ወደ ነፍሳችን መግባት ያስፈልገናል—2፡2፣ 5፤ 4፡2።

ለ. እውነተኛ በአንድ ልብ መሆን ይኖረን ዘንድ፣ "በአንድ ልብና በአንድ አሳብም" የተባበርን መሆን ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 1፡10፤ 7፡25፣ 40፦

1. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በአንድ ልብ መሆን እውን እንዳይሆንልን የሚገድበን ችግር አመለካከታችን ነው—ማቴ. 16፡22-25፤ ፊልጵ. 2፡2፤ 4፡2።
2. በጌታ ሥራ ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እና በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ታላቁ ጎጂ ምክንያት አመለካከታችን ነው—1 ቆሮ. 1፡10-13።
3. አመለካከቶች የጨለማ ምልክት ናቸው (ዮሐ. 11፡9-10)፤ ከጌታ ፈቃድ ጋር የሚቃረን አመለካከት በገለጥን ጊዜ ሁሉ ያ አመለካከት በጨለማ እየተመላለስን መሆናችንን ያመለክታል።
4. ጌታ በማንኛውም ሰው አመለካከት መሠረት ፈጽሞ አይንቀሳቀስም፤ ጌታ ሁልጊዜም የሚንቀሳቀሰው በገዛ ፈቃዱ መሠረት ነው፣ በአመለካከታችን መሠረት የሆነን ጸሎት ጨምሮ፣ በአመለካከታችን መሠረት ፈጽሞ አይንቀሳቀስም—1 ዮሐ. 5፡14-15።

ሐ. በአንድ ልብ መሆን በመላው ማንነታችን አንድ መሆን ነው፣ ይህም በውጫዊ ንግግራችን አንድ መሆንን ያመጣል—ሮሜ 15፡5-6።

1. አንድ ሃሳብ እና አንድ አፍ ያለው መሆን ትርጉሙ አንድ ራስ—ክርስቶስ—አለን ማለት ነው፣ ምክንያቱም ራስ የሆነው እርሱ ብቻ ሃሳብ እና አፍ አለውና፤ ማሰብ ያለብን በክርስቶስ ሃሳብ፣ መናገርም ያለብን ራስ በሆነው በእርሱ አፍ መሆን አለበት—ቆላ. 1፡18፤ ፊልጵ. 2፡2፣ 5፤ 4፡2።
2. በአንድ ልብ በሆንን ጊዜ ሁሉ አንድ ንግግር እንናገራለን፤ በአንድ አፍም እንናገራለን።
3. በአንድ ልብ እና በአንድ አፍ የመሆኛው ብቸኛ መንገድ፣ እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ በልባችን ውስጥ እና በአፋችን ክርስቶስ ሁሉ ነገር እንዲሆን መፍቀድ ነው—ኤፌ. 3፡17፣21።

## V. በአንድ ልብ መሆን በአዲስ ኪዳን ላለ በረከት ሁሉ ዋናው ቁልፍ ነው—ሐዋ. 1፡14፤ ኤፌ. 1፡3፤ ሮሜ 15፡29፦

ሀ. የእግዚአብሔርን በረከት እንደ ውድ መዝገብ መያዝ እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሁሉም ነገር የሚመረኮዘው በእግዚአብሔር በረከት ላይ እንደሆነ መገንዘብ አለብን—ኤፌ. 1፡3።

ለ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በእግዚአብሔር የታዘዘውን በረከት ሲቀበሉ ማየት እንፈልጋለን—መዝ. 133፡3።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ተግባራዊ ልምምዳችን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን "በክርስቶስ በረከት ሙላት" ሥር የምትሆንበትን መንገድ ማወቅ ያስፈልገናል—ሮሜ 15፡29፦

1. እግዚአብሔር የሚባርከው በአንድ ልብ መሆንን ብቻ ስለሆነ የእግዚአብሔር በረከት በአንድ ልብ በመሆን ሁኔታ ላይ ብቻ እንደሚመጣ መገንዘባችን ወሳኝ ነው—ሐዋ. 2፡46።
2. የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል አንድነትን በተግባር መለማመድ አለብን፣ አንድነትን በተግባር የመለማመድ መንገድ ደግሞ በአንድ ልብ መሆን ነው—4፡24፤ 15፡25፤ ሮሜ 15፡6።

© 2021 Living Stream Ministry